እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው ፤ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፋዋለች ትዕቢተኛ ዓይን ፤ ሐሰተኛ ምላስ ፤ ንጹሕን ደም የምታፈስስ እጅ ፤ ክፉ አሳብን የሚያበቅል ልብ ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር ፤ በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር ፤ በወንድማማች መካከል ጠብን የሚዘራ። (ምሳሌ ፮፥፲፮-፲፱)

## ይቅርታ ምሥጢር ነው።

ዳዊት ቀድሞ ባየው በአፍላገ ዮርዳኖስ፣
በዕደ ዮሐንስ ተጠምቀህ ክርስቶስ፣
አዳምን ባሳተው በሰይጣን ዲያብሎስ፣
ክርስቶስ ተፈተንክ ገዳመ ቆሮንቶስ።

ከሁሉም ይበልጣል ይኼ ፆም ታላቅ ነው
በምድር ሥጋ ለብሶ ፈጣሪ የፆመው።
፵ ቀን ፵ ሌት ገዳመ ቆሮንቶስ፣
ይኼን ፆም ፆሞታል ኢየሱስ ክርስቶስ።
አዳምን ሄዋንን በገነት ያሳተው፣
በበለስ አታሎ ከአምላክ የለያየው፣
ጌታንም በእንጀራ ቀርቦ ሊፈትነው፣
ገዳም መጥቶ ነበር ጥንት እንደለመደው።
በፆም ድል ማድረግን ጌታ አስተምሮናል፣
ሁሉ እንደ እምነታችን ይደረግልናል።

እኔም አንተም አንቺም ሁላችንም ዛሬ፣
የምንፆመው ፆም እንዲያሰጠን ፍሬ፣
በታላቅ ወንጌል ቃል ጌታ እንዳስተማረን፣
በይቅርታ እንጀምር ይቅር ተባብለን።
ቂም ይዘን እንዳንቆም ትናንትን አስበን፣
ዛሬ ሌላ ቀን ነው እንኑር ተስማምተን።

እንደ ጌሴም ምድር ክብርህን አሳየን፣
አቤቱ አባታችን እኛንም አስበን።
ከሁሉ የሚበልጥ አንተ ዘንድ የሚያደርስ
በውስጣችን አፍስስ የይቅርታ መንፈስ።
ታላቁን በረከት አባታችን ስጠን፣
ይህ ነው ጥያቄአችን ይቅርታህ ይድረሰን።
ከቤት ካልጀመረ ሰላምና ፍቅር፣
ውሸት ነው አይሆንም ጸጥ አትልም ምድር

በእኔም በአንተም በአንቺም የይቅርታ መንፈስ፣
በቤት በኑሮአችን በውስጣችን ይንገሥ።
የሰው ቃል አይደለም የፈጣሪ ቃል ነው
ይቅርታ ለሰው ልጅ ገንዘብ መድኃኒት ነው
በግብር እንፈጽም የወንጌልን ነገር፣
ይቅርታ ታላቅ ነው ለእርቅ እንደራደር

ሃያ ዓመታት ያህል በትዳር የኖረች፣
መካን በመሆንዋ መውለድ ስላልቻለች፣
ስለ ርብቃ ብሎ ጸሎት ላቀረበው፣
እግዚአብሔር ይስሐቅን ሰማው ተለመነው።
ተዘግቶ እንዳልነበር ማኅፀንዋ ተፈታ፣
ርብቃ ጸነሰች መካኒቱ መንታ።
ከአንድ ማኅፀን ውስጥ በአንድ ላይ የኖሩ፤
በዘጠኝ ወር ዕድሜ ጠብ ግፊያ ጀመሩ።
ገና በልጅነት ትንንቅ የገጠሙ፣
ዓመታት ሞላቸው አድገው ሳይስማሙ።

በሰው የደረሰው የጸብ አምባ - ጓሮ፣
ያዕቆብም ደርሶበት ተለያይቶ ኖሮ፣
ሃያ ዓመታት ያህል ወንድሙን ሳያየው፣
መታረቅን ነበር ቀድሞ የወሰነው።
ወደ ሴይር ምድር ወደ ኤዶም አገር፣
መልእክተኞች ላከ ያዕቆብ ሊደራደር።
ፍየል በግ አህያ ላም ግመል አውጥቶ፣
ለኤሳው የሚሆን እጅ መንሻ አዘጋጅቶ፣
ፈርቶ ተንቀጥቅጦ እራሱን አዋርዶ፣
ያእቆብ በሕዝቡ ፊት ባሪያ መባል ፈቅዶ፣
ወደሱ ሲመጣ ሊገናኘው ኤሳው፣
«ጌታዬ» በማለት አምስት ጊዜ ጠራው።
ያዕቆብ ኤሳውን ሲያይ ዓይኖቹን አንሥቶ፣
ይሰግድለት ጀመር ወደ ምድር ተደፍቶ።
የተሰበረ ልብ ይኼ ነው ይቅርታ፣
ቂም - በቀል የሌለው ልቡ የተፈታ።
የሰማንያ ዓመት ሰው ሰባት ጊዜ ሰግዶ፣
ይቅርታ ጠየቀ እራሱን አዋርዶ።

ያንን እንሻለን ዛሬም በምድራችን፣
የወንድማማች ነው ቅያሜ ጸባችን።
መሃናይም ብለህ በጠራኸው ስፍራ፣
መልካም ዜና ሰማህ ስለ ዕርቅ ተወራ።
እስከ ንጋት ድረስ ሌሊት የታገለህ፣
ምን ዓይነት ጸጋ ነው አምላክህ የሰጠህ።
ያዕቆብ ከአንተ እንማር ለእርቅ መደራደር
«ጌታዬ ነህ» ብሎ ባሪያ ሆኖ ማደር።
የአባቶችህ አምላክ የአብርሃም የይስሐቅ፣
ያዕቆብ ተለመነህ ልብህን ስለሚያቅ።

የሃያ ዓመታት ጸብ በሰላም ተፈታ፣
በእግዚአብሔር አገልጋይ በያዕቆብ ይቅርታ
እስኪ መፍትሄ አምጡ እኛስ ምን እንማር
ተስማምቶ ለመኖር ከተጣላነው ጋር።
በአፋችን አውጀን ሰላም ፍቅር አንድነት፣
«አሜን ይሁን» ብለን ኖረናል ብዙ ዓመት

ስለ ሰላም ሰብከን ስለ ፍቅር  አውርተን፣
ትናንትም ታይተናል ጸብ ጥላቻ አፍርተን።
የአምናው የታች አምናው የቀደመው ዘመን
ያለፈው   ይበቃል   የልዩነቱ   ቀን።
በአንድነት እንቁም በአፍ ሳይሆን በተግባር፣
ሰላምን   እናውጅ  ፍቅርን  እንማር።
ትንሹን  ንቀነው  ትልቁን  ደፍረነው፣
«ምን ያመጣል» ብለን ደሃውን ትተነው፣
ኖረናል ዝንተ ዓመት ቃል እያፈረስን፣
በሸንጎ   ፊት  ቆመን  እየተካሰስን፣
የልዩነት ዘመን እንዳይኖር ከእንግዲህ፣
እስኪ እኔና እናንተ እንጀምር ከእዚህ።
ጦር ሳይኖር በእጃችን ሰይፍና ስለት፣
ቂም በቀል ገደለን የማይሆን ልዩነት።
ወዴት ሊደረስ ነው ይብቃን መተላለፍ፣
እንደምን አቃተን ለፍቅር መሸነፍ።
ታሪክ አይበላሽ  ሃይማኖት አይጥፋ፣
ለምን  ይጨልማል  የነበረን  ተስፋ?
አንድ ሆነን እንኑር መናናቅ ይቅርብን፣
በራችን ክፍት ነው አብረን እናመስግን።
በመራራቃችን ደስ እንዳይለው ሰይጣን፣
የክርስቶስ ልጆች ፍቅር ነው የሚያዋጣን።

የይቅርታ ሰዎች አድርገን ክርስቶስ፣
በእምነት የምንጓዝ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ።
ገና ሳይረዳ  የራእዩን  ምሥጢር፣
ሂድ ብትለው ሄደ አንዳች ሳይጠረጥር።
እኛም የአንተ ልጆች ከጴጥሮስ ተምረን፣
ዛሬ ለመታዘዝ ዝግጁዎች አድርገን።

ታረቁ የሚል ወንጌል በእጃችን ጨብጠን፣
ኅብረት አልባ ሆንን መለየትን ወደን።
ድንገት ከተፍ ይላል ሞት የሚሉ እንግዳ፣
ተጣልተን እርስ በርስ ቤት ሳይሰናዳ።
አሁን ነው ማስተዋል መጠራት ሳይመጣ፣
ማንም ሰው አያውቃት ያቺን የጥሪ ዕጣ።
ፈጣን ነው ዘመኑ ቶሎ እያለፈብን፣
በዓለም ትርምስምስ ቃል ባክኗል ኅሊናችን
እርቅን ገንዘብ እናርግ ሁላችን በእመ አምላክ
የምሕረት መንፈስ ከእግዚአብሔር እንዲላክ
በአንድነት ተስማምተን ተዋደን እርስ በርስ
ወደቀደመችው   ፍቅር  እንመለስ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!

አብርሃም ሰሎሞን!!

የካቲት ፲፩/፳፻፩ ዓ.ም.